የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መጋቢት 2000

# ኢፖእአኮ 13 ዓመቱን አከበረ

ኢፖእአኮ ከተመሰረተ 13 ዓመቶች ያለፉ ሲሆን በዚህ ረጅም ጊዜ ድርጅቱ ዓላማዬ ብሎ የተነሳበትን ግዳጅ በስራ ለማዋል ታግሎ ውጤትን ማስመዘገቡ ተመስክሮለታል፡፡ ኢፖእአኮ የተቋቋመው በኢትዮጵያ ይካሄድ የነበረውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ ለማጋለጥ ሲሆን በተለይም በሌሎች የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች የተረሱትን የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይና ጩኸት ለዓለም ለማቅረብ ነበር፡፡ በዚህ መስክ ኢፖእአኮ የማይናቅ ስራን ሰርቷል ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

አፓእአኮ በርካታ መግለጫዎችን ሲያወጣ በተለይም በህዳጣን፤በሴቶችና ህፃናት ላይ አገዛዙ እየፈፀመ ያለውን መብት ረገጣ በሰፊው አጋልጧል፡፡ ወደ መካከለኛ ምስራቅ ተጉዘው መከራና ፍዳ እየቀመሱ ያሉትን ወጣት ሴቶችንም ሰቆቃ ሆነ በጎረቤት ሀገሮች የሚሰቃዩትን ስደተኞች መከራ በይፋ በማቅረብ የመብት ረገጣው እንዲቆም ታግሏል፡፡ ኢፖእአኮ ባለፉት 13 ዓመታት ሊቀጥል የቻለው በአባላቱና ደጋፊዎቹ ድጋፍ ቢሆንም ሊያጠፉት የተካሄዱትን ሴራዎች ሳይጠቅስ ቢያልፍ ትክክል አይሆንም፡፡ በሀገር ቤት ሆኖ ለኮሚቴው በአባልነት ሙሉ ድጋፍ ይሰጥ የነበረው ተስፋዬ ታደሰ በአገዛዙ ተገድሏል፡፡ የአገዛዙ ተቀጣሪዎችና ደጋፊዎች በኮሚቴው ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ባለማቋረጥ አካሂደዋል፡፡ በቶሮንቶ ካናዳ ደግሞ ጥቂት ግለሰቦች የኮሚቴውን ስም በህገወጥ መንገድ እየተጠቀሙ ሊያደናግሩ ሞክረዋል፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም መሰናክሎች ተወጥቶ ኮሚቴው ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ተጠናክሮ በመቀጠል ላይ ነው፡፡ ይህ ለወዳጅ የሚያስደስት ዜና ሲሆን ለጠላቶቹ ደግሞ መርዶ ነው፡፡ በዚህም አጋጣሚ ኮሚቴው ድጋፍና ትብብር ለሰጡት ሁሉ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

ኢፖእአኮ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ አባላቶች ያሉት ሲሆን በሰብዓዊ መብት ረገጣ ላይ ዘገባና መረጃ የሚልኩለት ብዙ ናቸው፡፡ በአገዛዙና ደጋፊዎቹ የተከፈተበትን ልዩ ልዩ አፍራሽ ጥቃትንም እየተቋቋመ ነው፡፡ ስብሰባ አካሂዶም በአሜሪካና ካናዳ፤በአፍሪካ፤አውሮጳ፤ በኦሺያኒያና ኢትዮጵያ ተጠሪዎቹን መድቦ በአዲስ መንፈስ እንቅስቃሴውን ቀጥሏል፡፡ በሌሎች የሰብዓዊ መብት ረገጣ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶች በሰበብ አስባቡ የተረሱትን የፖለቲካ እስረኞችና ደብዛቸው የጠፋውንም ዜጎች ጉዳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ አጋልጦ እንዲታወቅ አድርጓል፡፡ ኮሚቴው በስራው ሊኩራራ ባይቃጣውም ባለው ውሱን አቅም የሰራው ግን የሚያስመሰግን መሆኑ በግድ መጠቀስ ያለበት ነው፡፡

ኢፖእአኮ የዜጎችን አርዳታ ካላገኘ ለመቀጠል ያስቸግረዋልና ሁላችሁም ትረዱት ዘንድ አደራ ይላል፡፡ የቼክ ወይም መኒ ኦርደራቸሁን ለ ሶሴፕ ብላችሁ በሚቀጥው የባንክ አድራሻ ላኩልን፤

**SOCEPP Bank Account no. 1281468-90**
**Commerzbank AG (BLZ 37040044)**
**Hohenzollernring 71-73**
**50762 KOLN, GERMANY.**

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
E mail :socepp@aol.com WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE